# ህልውና ሲሉ ህልውና ስንል!

ጥቅምት 3 ቀን 2019ዓም( 13-10-2026)

በመጀመሪያ ህልውና የሚለውን ቃል ፍች እንመልከተው።የመኖር ዋስትና፣ዕድል ወይም የወደፊት እጣ ፈንታ፣('Existence,Desstiny) ማለት እንደሆነ እንረዳለን።የሰው ልጅ ስላለበትና ወደፊት ስለሚኖረው ኑሮ ማሰቡና መጨነቁ የተፈጥሮ ግዴታው ነው።በችግር ውስጥ የሚኖር ከድህነት የሚላቀቅበትን፣በበሽታ የሚሰቃይ የሚድንበትን ፣በአምባገነኖች መዳፍ የሚማቅቅ ሕዝብ ነጻነት፣ፍትሕ፣እኩልነት በሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚኖርበትን መንገድ የማሰላሰሉና የመከተሉ ውሳኔ ከጥያቄ ውስጥ የሚገባና የሚቃወሙት አይሆንም። ከዚህም ባሻገር የአንድ አገር ሕዝብ አንድነቱና ሰላሙ ሲናጋ፣በጎሳና በሃይማኖት ሰልፍ ውስጥ ገብቶ እርስ በርሱ ሲጋጭና ሲጨፋጨፍ ብሎም ተበታትኖ አገር አልባ የመሆን አደጋ ሲደቀንበት የራሱንና የአገሩን ህልውና ለማስጠበቅ ይነሳል።ለመበታተን ምክንያት የሆኑትን ጸረ አንድነትና ጸረ አገር የሆኑትን ይፋለማል፤ድንበር ጥሶ የመጣውን ጠላትና በውስጥ ተባባሪ የሆነውን ባንዳ ይከላከላል። በዚህ መስፈርት አኳያ አሁን በአገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ በህልውና ስም የሚካሄዱ ትግሎች ጎልተው ይታያሉ።

1/ በማንነታቸው የተገፉ፣ ሰብአዊ መብታቸውንና ክብራቸውን የተገፈፉ፣በሚከተሉት ሃይማኖትና በሚይዙት የፖለቲካ አስተሳሰብና አቋማቸው የሚጠቁና የሚገለሉ፣ ለእኩልነትና ለዜግነት መብታቸው ሲሉ የህልውና ትግል ያደርጋሉ።ለነሱ ህልውና ማለት እኩልነትና ፍትህ፣ አንድነትና ሰላም የኢትዮጵያ አገራቸውም ልዑላዊነት ነው።በእዚህ ትግል ውስጥ የሚሳተፉ በኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው ላይ የሚዘምቱ ሳይሆኑ በተዛባውና አምባገነናዊ ብሎም የጠባብ ጎሰኞች መፈንጫ በሆነው ስርዓት ላይ የተነሱና በእኩልነት ከሌላው ወገናቸው ጋር አብሮ ለመኖር የሚሹ ናቸው። በታሪካቸው የሚኮሩ፣በአንድ አገር ልጅነታቸው የሚያምኑና የአንድ አገር ምልክት የሆነውን አንድ ሰንደቅ ዓላማ የሚያውለበልቡ ፣ለአገራቸው ዳር ድንበር የተሰዉና ለመሰዋት የማይግደረደሩ፣ለውጭ ጠላት የማያጎበድዱ፣ በአገር ልዑላዊነት የማይደራደሩ፣ያገር ህልውናን ለጠላት ዳረጎት የማይሸጡና አሳልፈው የማይሰጡ፣አገራቸውን ለጥቃትና ለወረራ የማያጋልጡ፣አገራቸው አድጋና መንድጋ ዜጎቿ ከችግር፣ ከርሃብ፣ ከበሽታና ከኋላቀርነት ተላቃ የምታኮራ አገር እንዲኖራቸው የሚፈልጉ አገር ወዳዶች ናቸው።ከራሳቸው አልፎ ለመጭው ትውልድ የተመቸች አገር ለማስረከብ የቆረጡ፣ስደትንና ልመናን ታሪክ ለማድረግ የሚፈልጉ የራስ መተማመን ስሜት የተላበሱ ፣ለራሳቸው አገር ቀርቶ ለሌላው አገር ሕዝብ ሰብአዊ መብት፣ ደህንነትና ሰላም የሚያስቡ፤ ድንበር ተሻጋሪ ስብእና ፣ዘመናዊና ተራማጅ ዓለም አቀፋዊ እይታ ያላቸው ናቸው።

2/ በሌላው የህልውና ጎራ የተሰለፉት ደግሞ የመጀመሪያው ተቃራኒ በሆነው እረድፍ የሚቀመጡት ናቸው። ለእነሱ ህልውና ማለት ከጠባብ የግልና የቡድን ፍላጎት ያላለፈ፣ለሥልጣንና ለጥቅም ሲባል አገርና ሕዝብን ቀብድ የማስያዝ ፍላጎትና ልምድ ያላቸው።በጠባብ ጎሰኝነት የአገርን ትልቅ ዳር ድንበር በከባቢ ጠባብ ኬላ የሚተኩ፣ከአንድ ትልቅ አገር ይልቅ የብዙ ደቃቃ መንደሮች ባለቤት ለመሆን የሚሹ፣ከአንድ ትልቅ ብሔራዊ ማንነት ይልቅ በቋንቋና በሃይማኖት እረድፍ የተበታተነ ዜጋና የሚኖርበት ቀጫጫ አገር ማንነትን የሚመርጡ፣ ለአንድነት ምልክት የሆነ አንድ የጋራ ሰንደቅዓላማ ከማውለብለብ ይልቅ ዝብርቅርቁ የወጣ ባንዲራ መሸከምን የነጻነትና የእኩልነት ምልክት አድርገው የሚቆጥሩ፣ለሚፈልጉት ዓላማ የሚተባበራቸው ከሆነ ከማንኛውም የውጭ ጠላት ጋር ለመሰለፍ የማያቅማሙ፣የጠላቴ ጠላት ብለው አገራቸውን ለባዕድ አሳልፈው የሚሰጡና መጠቀሚያ የሚሆኑ ናቸው።

በአጭሩ የህልውና ትግል በነዚህ ከላይ በተጠቀሱት መልኮች የሚገለጽ ሲሆን ባጭሩ የኢትዮጵያ ህልውናና የጸረ ኢትዮጵያ ወይም የተገንጣዮች ህልውና ተብሎ ሊመደብ ይችላል።

ሌላው ማንኛውም የህሊና ትግል ከሂስና ከጥያቄ ነጻ ሊሆን አይችልም።ግልጽነት የሌለው፣የመጨረሻ ግቡ ምን እንደሆነ የማይታወቅና ተሸፋፍኖ የሚቀርብ ከሆነ ፣ ሊጠዬቅና ስህተትም ሲሠራ ለተቃውሞ ዝግጁ መሆን ይኖርበታል። የተቃውሞ በሮችን ክርችም አድርጎ የሚዘጋ፣ በማን አህሎኝነት ለማስበርገግና በልዩ ልዩ

ስያሜዎች በማሸማቀቅ ድምጽን ለማፈን የሚነሳ ከሆነ ከሁለተኛው የህልውና ትግል ተሰላፊዎች የተለዩ አይሆንም።ህልውናው አምባገነንነትን ለማሶገድ ሳይሆን ለመተካት ነው ማለት ነው።

ሲደመርና ሲቀነስ በሥልጣን ላይ ያለው የጎሰኞች አገዛዝና በጫካ ያለው የጎሰኞች ስብስብ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች መሆናቸውን እያዩን መጥተናል።ሁለቱም ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሚል ማንነትን የሚያስተጋቡ፣ክልልና እራስን በራስ የማስተዳደር እስከ መገንጠል ድረስ የሚለውን መብት በአንቀጽ 39 የደነገጉ መሆናቸው የሚያመሳስላቸው እንጂ የሚለያያቸው አይሆንም። ጠባቸው የሥልጣንና የጥቅም ወይም የሚሄዱበት ስልትና ፍጥነት ብቻ እንጂ የዓላማ አለመሆኑን ያሳያል።

በተገንጣዮቹ በኩል ሕዝቡን ለማማለል "ሁሉን ያካተተ የሽግግር መንግሥት እናቋቁማለን" የሚል ማታለያ ተነግሯል። ይህ እንመሠርተዋለን የሚሉት የሽግግር መንግሥት ከ33 ዓመት በፊት በወያኔ በሻእብያና ኦነግ ተመስርቶ የኤርትራን መገንጠል የፈቀደውን የሚመስልና አሁን በህልውና ስም የተሰባሰቡት በተራቸው ተገንጥለው እንዲሄዱ ሕጋዊ ሽፋን የሚሰጥ የዳግም ማጭበርበር ስልት ሊሆን እንደሚችል ማወቅ ይገባል። በታጠቀ ቡድን የሚመሠረት መንግሥት በምንም መልኩ ዴሞክራሲያዊ አይሆንም።የሥልጣን ወንበሩንም ለሕዝብ ተወካይ አሳልፎ አይሰጥም። አስተማማኝ የሽግግር መንግሥት ነጻ በሆኑ አገር ወዳድ ሙያተኞች ቢመሠረት ሕግና ስርዓትን በማስከበር አስተማማኝና የተሻለ ለዘላቂው ቋሚ መንግሥት ፈር ቀዳጅ ይሆናል። ከዚያ በተረፈ በጎሰኛና በተገንጣዮች በኩል የባሰ እንጂ ምንም የለውጥ ጭላንጭል አይመጣም፤ያንንም ባለፉት 35 ዓመታት አይተነዋል።እግር ወዲያ ሄዶ እግር መጣ ወዲህ ወይም ስልቻ ቀልቀሎ ቀልቀሎ ስልቻ ማለት ነው።

የአገር ወዳዶቹ ና የተገንጣዮቹ ህልውና በነዚህ በሁለቱ መካከል ያለ ትርጉም ያለው ህልውና ነው። ተገንጣዮች መገንጠልን ህልውና ብለው ሲነሱ አገር ወዳዶች ደግሞ ኢትዮጵያዊነት ህልውናችን ብለው ለአንድነት ይነሳሉ።የአገር ወዳዶች ዝምታና አለመሰባሰብ ለተሰበሰቡት አገር ጠሌዎች ጉልበትና የሞራል ድጋፍ ይሆናቸዋል።ስለሆነም አገር ወዳዱ ደፍሮ መነሳት ይኖርበታል። አገራችን ከለዬለት አሮንቋ ከመግባቷ በፊት የምትድንበትን መንገድ መሻትና በተግባር መግለጽ ሕዝቡንም ማንቃትና በአንድነት እንዲቆም ማድረግ ለነገ የማይባል ድርሻ ነው።

ሻእብያን መቃወም የኤርትራን ሕዝብ መቃወም አይደለም።ወያኔን መቃወም የትግራይን ወገናችንን መቃወም አይደለም።ኦነግን ና ብልጽግናን መቃወም ኦሮሞና ሌላውን ወገናችንን መቃወም አይደለም።ሌሎቹንም ነጻ አውጭ ነን ባዮች መቃወም በስሙ የሚነግዱበትን ወገናችንን መቃወም አይደለም። ኢትዮጵያ አንዱን ጥላ ሌላውን አንጠልጥላ ልትኖር አትችልም።ትልቁ ጎሳ ትንሹን ጎሳ ውጦና ተጭኖ ሊኖር አይገባም።በቁጥር መብለጥና ማነስ ሰብአዊ ፍጡርነትን አይቀንስም ወይም አያሳድግም፤ለዜግነትም መለኪያ ሚዛን አይሆንም።። ሁሉም ኢትዮጵያዊ አነሰም በዛም፣ቀላም ጠቆረም እኩል የአንድ አገር ዜጋ ነው።ከፉና ደጉን አብሮ የተካፈለና በመካፈልም ላይ ያለ ሕዝብ ነው።በስሙ በሚነግዱ ነጻ አውጭ ነን ባዮች እኩል ይሰቃያል።ያለው አማራጭ በስማችን የሚነግዱትን ቡድኖች ከጫንቃችን ላይ አውርደን የኢትዮጵያን አገራዊ ክብርና አንድነት በሚያስጠብቅ ፍትሕና ዴሞክራሲን ስርዓት ለሚያሰፍን ፣ከጠባብ ክልል ወጥተን የትልቅ አገር ባለቤት ለሚያደርገን ለጋራ ማንነታችን ለኢትዮጵያዊነታችን ህልውናችን መሰለፍ ብቻ ነው።

አሁን ላይ ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑት የውጭ ሃይሎች በተለይም የጎረቤት አገሮች ግብጽ ሱዳን ኤርትራና ሶማሊያ መሪዎች በግብጽ አል አሜይን በተባለ ከተማ ውስጥ ተሰብስበው በኢትዮጵያ በተለይም በአባይ ወንዝ ላይ የጋራ አቋም ወስደዋል።እንደነሱ አቋም አባይ ወንዝ ላይ የመወሰን መብት አለን ባዮች ናቸው፤ያም ከእኛ ፈቃድ ውጭ ኢትዮጵያ እንዳሻት ግድብ መሥራት አትችልም፣ለልማትና ለእድገት መነሳት የለባትም በድህነትና በልዩነት እየማቀቀች ትኑር የሚል የተዛባ፣ጠላትነት በግልጽ የሚያንጸባርቅ አቋም ነው።ሱዳንና ግብጽ በሚያቋርጣቸው በአባይ ውሃ ላይ ያሻቸውን ሲያደርጉ ኢትዮጵያን መነሻው ባደረገው አባይ ወንዝ ላይ የመከልሉ ነገር ሕጋዊነት የለውም፤ ለኢትዮጵያኑ ብቻም ሳይሆን ለፍትሕ ለሚቆምየዓለም ማህበረሰብ የሚዋጥለት አይሆንም።ያiteዮጵያ አባይን ትጠቀም ሲባል ግን አገራችን ኢትዮጵያ የራሷን ጥቅም አስከብራ

የሌሎችንም ጥቅም ትጋፋ ማለት አይደለም።አባይ የተፈጥሮ ጸጋ ነው።በሰዎች እጅ የተሠራ አይደለም። ከኢትዮጵያም አልፎ ለሱዳንና ለግብጽ ሕዝብ የመኖራቸው ዋስትና ነው።ያንን ከግንዛቤ አስገብቶ ሁሉም ተጠቃሚ የሚሆንበትን መንገድ መፈለግ ተገቢ ነው።በአንዱ ኪሳራ ሌላው ሊኖር አይገባውምና!

አሁን ላይ እንደሚታዬው ከሆነ ግን አራቱ አገራት ኢትዮጵያ የገባችበትን ምስቅልቅል ሁኔታና አለመረጋጋት ተጠቅመው ፍላጎታቸውን ለማሳካት ተባብረው መነሳታቸውን ታዝበናል።ይህ የመጀመሪያ ሳይሆን ተዳጋጋሚ ክስተት ነው።ኢትዮጵያ በቀውስ ውስጥ ስትገባ፣ደካማና ልፍስፍስ ብሎም ሕዝብ የሚቃወመውና የጠላው አገዛዝ ሲኖር አንገታቸውን ቀና ማድረጋቸው የተለመደ ክስተት ነው።በወታደራዊ አምባገነኑ የደርግ አገዛዝ ዘመን ሶማሊያን ከፊት አሰልፎ ጦርነቱን ሲያፋፍም የነበረው ይኸው በግብጽና በሱዳን መንግሥታት ተባባሪነት የተፈጠረው ግንባር ነበር።

በዚያን ጊዜ ከኢትዮጵያ ተገንጥለን አገር እንመሠርታለን ብለው የተነሱትን ሻእብያን፣ህወሃትን(ወያኔን)ና ኦነግን የውስጥ ተባባሪ በማድረግ በኢትዮጵያ ላይ ጥምር ዘመቻ አካሂደዋል።ከሞላ ጎደል ተሳክቶላቸውም ኤርትራን አስገንጥለው ኢትዮጵያን ወደብ አልባ አድርገዋታል።ለዘመናት በታሪክ በእምነት በባህልና በፊደል እንዲሁም በመዋለድ በእትብት የተሳሰረን ሕዝብ ለመቆራረጥና በጠላትነት እንዲተያይ አድርገውታል።ወያኔም ለ27 ዓመታት በሥልጣን ላይ ተቀምጦ ያሻውን እንዲያደርግ ፈቅደውለታል።

የ27 ዓመት ያገዛዝ ወንበሩን በሕዝብ ትግል የተነፈገው ህወሃት(ወያኔ) አኩርፎ ትግራይ ሲገባና ጦርነት ሲከፍት እነዚሁ አገሮች ሌሎቹም ያውሮፓ አገሮች የመሣሪያና የሎጅስቲክስ ድጋፍ በማድረግ በእጅ አዙር የጦርነቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል።ከብዙ ደም መፋሰስና የብዙ ኢትዮጵያውያን ህይወት ከጠፋ በኋላ በአገዛዙ የበላይነት ጦርነቱ ሲጠናቀቅ ዳግም ጦርነት እንዳይነሳ በአፍሪካና በተባበሩት መንግሥታት ተሳትፎ በደቡብ አፍሪካ በፕሪቶሪያ ከተማ የስምምነት ሰነድ ለመፈራረም በቁ። ሆኖም ግን ህወሃት(ወያኔ) በዚያ ባለመርካቱ ማለትም ለመገንጠልና እንደ አገር ለመኖር ይረዳኛል ያለውን በትግሉ ወቅት መውጫና መግቢያ ይሆነኛል ብሎ የተቆጣጠረውን የኢትዮጵያ ለም መሬት ወልቃይትንና ራያን በይገባኛልነት ለዳግም ግጭት መነሻ ምክንያት አድርጎ መንቀሳቀስ ጀመረ።ለአጭር ጊዜ የጋብቻ ቀለበት ያሰሩትም ኢሳያስና አብይ አህመድ ጠብ ውስጥ ገቡና ለአዲስ ጦርነት አዲስ ሰልፍ ተጀመረ።እነዚያው ግብጽና ሱዳንም ሌሎቹን ሶማሊያንና ኤርትራን ጨምረው አራት በመሆን ዳግም ግንባር ፈጥረው ቆሙ።

በዚህ ጸረ ኢትዮጵያ የጋራ ግንባር ውስጥ አዲስ ክስተት የሆነው የብልጽግናን አገዛዝ በመቃወም በአማራው ስም የተቋቋመው ፋኖ የተባለው ታጣቂ ቡድን አንደኛው ክንፍ ተባባሪ ሆኖ መገኘቱ ነው።"ትብብር ለህልውና"በሚል ጭንብል ከህወሃት ሻእብያና ኦነግ እንዲሁም መሰል ተገንጣይ ሃይሎች ጋር በመጣመር በእጅ አዙር ማለትም በኤርትራ በኩል የሱዳንና የግብጽ ጉዳይ ፈጻሚ ሆኖ ተሰልፏል።ይህንን በተመለከት በፋኖ ውስጥና ውጭ መከፋፈልና ተቃውሞ ቀስቅሷል። ለአገር አንድነትና ልዑላዊነት ብሎም ለሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ይታገላል ተብሎ ከሚታሰብ የአማራ ሃይል እንዲህ አይነቱ ክህደት ሲፈጸም ማዬት ያሳዝናል።ማዘንም ብቻ ሳይሆን አምርረው የሚቃወሙትና የሚታገሉት ሊሆን ይገባል።በዓላማቸው ጸንተው የቆሙትን እውነተኛ የፋኖ ሃይሎች በማጠናከር ለታለመው ስር ነቀል ለውጥ ከመሰለፍ የተሻለ ምርጫ የለም። ጎሰኝነትን እስከነአካቴው ማሶገድ እንጂ እንዲቀጥል መፍቀድ ጸረ ኢትዮጵያ መሆን ነው።ለዛም ከነጠላ ጎሳ ትግል ህብረብሔራዊ የሆነ ትግል ማድረግ ይመረጣል።የአማራ ፋኖ ከማለት የኢትዮጵያ ፋኖ ብሎ መንቀሳቀሱ ትግሉን አገር አቀፋዊ ያደርገዋል።የአድዋንም የአንድነትና የድል መንፈስና ቁመና ያላብሳል። ,

ሌላው መዘንጋት የሌለበት ጎሰኞች ባመጡት ጣጣ የሚቀሰቀሰው ጦርነት በሕዝብ ላይ እልቂትን በአገር ላይ ድቀትን ሲያስከትል መቻሉንና ለመሣሪያ ነጋዴዎቹ የገቢ ምንጭ እንደሚሆናቸው ነው። በእኛ መተላለቅ የመሣሪያ ችብቸባቸውን ያጧጡፉታል። ደጋፊና ተቆርቋሪ በመምሰል ያዞ እምባቸውን እዬረጩ በእኛ ጅልነት ይሳለቃሉ።ከዛም አልፎ ተርፎ በተገንጣዮቹ ጀርባና አንቀልባ ዘው ብለው ገብተው ያሻቸውን ያደርጋሉ። ለሸጡት መሣሪያ ያገር ንብረትና የተፈጥሮ ሃብት በወለድ አግድ ይይዛሉ።የዳግም ቅኝ አገዛዛቸውን በእጅ አዙር መልክ ያረጋግጣሉ። ከሞኝ ገበሬ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል እንዲሉ!

ሌላው ድክመት በአገራችን ጉዳይ ላይ የውጭ አካል ጣልቃ እንዲገባ መፍቀዱ ነው።የፕሪቶሪያው ስምምነት በሚል የድርድር ሰነድ ውስጥ ኢትዮጵያንና ትግራይን ሁለት የተለያዩ አገሮች የማድረግ አካሄድ ይታይበታል። ትግራይ የኢትዮጵያ ክፍለሃገር እንጂ እራሷን የቻለች ነጻ አገር አይደለችም።ሰነዱ ግን የትግራይና የኢትዮጵያ በማለት የሁለት አገሮች ግጭት አስመስሎ አቅርቦታል።የወልቃይትና ራያን መሬትም የትግራይ ይዞታ መሆናቸውን ተቀብሎ ከወያኔ ፈቃድ ውጭ ኢትዮጵያውያን በነጻነት የማይኖሩበት መሬት የማድረግ አዝማሚያ ይታይበታል።የቀድሞ ነዋሪዎች ተመልሰው ይኑሩ በሚለው የወያኔ ስልት ከባቢው በወያኔ ቁጥጥር ስር ስንዲውል ፣ቦታውንም ምዕራብ ትግራይ በሚል ስያሜ መጥራት ከሚስተዋሉት የእውቅና መንደርደሪያዎች እንደ አንዱ ሆኖ ይቆጠራል። ይህ ለወያኔ ለመገንጠል የሚያስችል አቅምና እውቅና ፈጥሯል። መታወቅ ያለበት የትግራይ ሕዝብም ኢትዮጵያዊ እንጂ ትግራይ የሚል ነጻ አገር ዜጋ አይደለም። በተገንጣዩ የወያኔ ቡድን የታገተ ሕዝብ ነው።የኦሮሞውም የሌላውም ኢትዮጵያዊ እንዲሁ በስሙ በተነሱ ተገንጣዮች የታገተ ሕዝብ ነው።አገር ወዳዱ ከተደራጀና ከታገለ የታገተው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነጻ ይወጣል። በስሙ የሚነግዱትም ተገንጣዮች ብትንትናቸው ይወጣል።ያንን አደጋ ለመቀልበስ ተገንጣዮቹ ህልውና ብለው የሰባት አገር ባንዲራ ተሸክመው በአንድ ላይ ሲቆሙ አገር ወዳዱም በራሱ የኢትዮጵያዊነት ህልውና ጣራ ስር አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ሰንደቅ ዓላማውን ከፍ አድርጎ በማውለብለብ መሰባሰብ አለበት።በትብብር ለሕልውና በሚለው ስር የተሰለፉት የፋኖ ቡድኖች ከስህተታቸው ተምረውና ይቅርታ ጠይቀው ከስብስቡ መለዪታቸውን ይፋ ካደረጉ የኢትዮጵያኑ ጎራ የይቅርታ በሩን አይዘጋባቸውም።ሆኖም ግን ተመልሰው በአመራር ቦታ ላይ ለመቀመጥ ሳይሆን በተራ ተዋጊነት ሊሰማሩ እንደሚችሉ ካልፈለጉም ከትግሉ ሜዳ ሊሰናበቱ እንደሚችሉ በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል።

አሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ የደረሰው ቀውስ የዓለምን ሕዝብ ለተቃውሞ እዬቀሰቀሰው ነው።በተለይም ወጣቱን ለተቃውሞ ባደባባይ እንዲውል አድርጎታል። ቀደም ሲል በኬንያ አሁን ደግሞ በፈረንሳይ፣ በቤልጅዬም ፣ በስፔይን የተማሪዎችና የሠራተኞች ተቃውሞ በኔዘርላንድም የሠራተኛው መደብ ተቃውሞ መንግሥታቱን ወጥሮ ይዟቸዋል። ነገሩ በቀላሉ የሚበርድ አይመስልም።በኑሮ ውድነት፣ በመኖሪያ ቤት እጥረትና በነዳጅ ውድነት አገራት እዬታመሱ ነው። ይህ ባለበት ሁኔታ መንግሥታቱ የጦር መሳሪያ ውድድር ላይ ናቸው። ከትምህርት ከጤና ከሌላውም መስክ ላይ ባጀት እዬቀነሱ ለጦር መሣሪያ ማዋላቸው ማህበራዊ ቁጣን ቀስቅሷል።የጦርነት ነጋሪት እዬተጎሰመ ነው።በተለይም በራሽያና በኡክሬን መካከል የሚካሄደው ጦርነት ለመሳሪያ ነጋዴ አገሮች ጥሩ አጋጣሚ ሆኖላቸዋል።ያባብሱታል እንጂ እንዲቆም አይፈልጉም።በጦርነት ወቅት መሣሪያ እዬሸጡ ከጦርነት በኋላም በግንባታ ስም ለመበዝበዝ ጉዳቱና ውድመቱን ይፈልጉታል።አልፎ አልፎም በኔቶ አባል አገሮች ድንበርና ሃብት ላይ ፍንዳታ በመፈጸም ጣታቸውን ወደ ሩስያ በመጠቆም ጦርነቱን የኔቶ አባል አገሮች ጦርነት ለማድረግ የሚጎነጎነው ሴራ ቀላል አይደለም።ይህ ሁኔታ ከቀጠለ ወደ ዓለም ጦርነት ላለመገባቱ ዋስትና የለም።ያ ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ባሉት የአፍሪካ አገሮች ላይ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ይሆንባቸዋል።

በኤሽያ አገሮች ወጣቱ አሻፈረኝ ብሏል።በላቲን አሜሪካም እንዲሁ።በያቅጣጫው የብሶት ድምጽ እያስተጋባ መጥቷል።የኢትዮጵያ ወጣት ከሌላው አገር ወጣት የተለዬ አይደለም ።የጊዜ ጉዳይ ነው የሚመራው ካገኘ እሱም እንደ የካቲቱ 66 ዓመተምህረቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እጅ ለእጅ ተያይዞ ለለውጥ ፋና ወጊ የሆነ የአደባባይ ትግሉን የሚያቀጣጥልበት ጊዜው እሩቅ አይሆንም።እንቅስቃሴው አቅጣጫውን እንዳይለውጥና የትግሉን ፍሬ እንዳይነጠቅ ግን ካለፉት ተምሮ አስተማማኝ ቁመና ላይ መገኘት ይኖርበታል።ሕዝባዊ የትግል ማእከል መፍጠር አለበት።በውጭ ያለው አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊም ያለበት ሁኔታ አመች ስለሆነ ትግሉ ስኬታማ እንዲሆን የምክርና ብሎም የዲፕሎማሲ እርዳታ ሊያደርግ ይገባዋል።በተለያዩ የቡድን ስም ከመቆም በአንድ አገር ወዳዶች ጣራ ስር መሰባሰብ ይኖርበታል።ተከፋፍሎ አይከፋፍል፤የአንድነት ምልክት ይሁን። ጎሰኝነትና ጎጠኝነት ለአገረ ኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት ነቀርሳ ነው።የኋላ ቀርነት ምልክት ነው።

ህልውናችን ኢትዮጵያዊነታችን!

አገሬ አዲስ